# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
# Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

## የኢሕአፓ ልዩ ጉባዔ ተጠናቀቀ

በተለያዩ ድርጅታዊ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ ለመስጠት ከጥቅምት 15 ቀን እስከ ጥቅምት 18 ቀን 2000 ዓም ድረስ ከልዩ ልዩ ቦታዎች የመጡ የአባላት ወኪሎች የተሳተፉበት ይህ ልዩና አስቸኳይ ጉባዔ፥ የፓርቲ አባላት በአፀደቋቸው አጀንዳዎች ላይ ውይይቶች አካሂዶ ልዩ ልዩ ውሳኔዎችን አሳልፏል።

ጉባዔው አራተኛው የፓርቲ ጉባዔ ያሳለፋቸውን ውሳኔዎች መርምሮ ተገቢነታቸውን እንደገና አስረግጦ የድርጀቱን መሪዎችንም መርጧል። ይህ የአባላቱን የትግል መንፈስና ወኔ በማያወላውል መልኩ ያስረገጠው አስቸኳይ ጉባዔ፥ የወያኔን አገዛዝ ከሀገራችን ሕዝብ ጫንቃ አሽቀንጥሮ ለመጣልና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለማምጣት የሚታገለውን የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረትን በማጠናከርና በህብረት ትግሉ ውስጥ ሌሎች ኃይሎች የሚካተቱበትን ሁኔታ አመቻችቶ ትግሉን ማፋፋም አስፈላጊ መሆኑን አምኗል። ማለትም የተቃዋሚ ሀይሎችን የትግል አንድነት ከሚሹ ኃይሎች ጋር ለመተባበር ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ፥ አማራጭ እንደሌለው ጉባዔው አረጋግጧል። በመሆኑም የወያኔን አገዛዝ አስወግዶ ሀገራችን ኢትዮጵያን ከጥፋት ለማዳን የሁሉም ኃይሎች መተባበር፥ ወሳኝነቱን አምነው ለሚታገሉ ሁሉ በጋራ የመታገል ጥሪውን ያስተላልፋል።

ይህ ታሪካዊ ጉባዔ በሚካሄድበት ወቅት በአራተኛው ጉባዔ አቅዋማቸው በብዙሀን ድምፅ ውድቅ የሆነባቸውና ከድርጅቱ ህግ ውጪ የተሰባሰቡ ውህዳን ተሳታፊዎች ጉባዔው ሳይጠናቀቅ ጉባዔውን ረግጠው ወጥተዋል። በድርጊታቸው ከማዘንና ከመገረም በስተቀር ጓዶቻችን ነበሩና፥ አብረን የጀመርነውን ትግል አብረን ከግቡ ለማድረስ፥ የተሰዉት ጓዶቻችን የትግል ቃል ኪዳንና አደራ አለ ሲለ ጉባዔው አምኗል። በመሆኑም ወደ ድርጅቱ ተመልሰው በመግባት ሀገራችንና ሕዝባችንን ከወያኔ አምባገነን ሥርዓት ነፃ ለማውጣት ትግሉን በጋራ እንዲቀጥሉ፥ ጉባዔው ጥሪ አስተላልፏል። ይህንንም ለማገዝ አንድ ኮሚቴ እንዲቋቋም ጉባዔው ወስኗል።

ሀገራችንን ከአምባገነኑ አገዛዝ ጭቆና አላቀን ፥ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የተመሠረተባት፥ የዜጎቿ ነፃነት የተረጋገጠባት፥ የግዛት አንድነቷና ብሔራዊ ልዕልናዋ የተከበረባት፥ ፍትኅ-ርትዕ የሰፈነባት ሀገር ዕውን እስክትሆን ድረስ ትግሉ የሚጠይቀውን ማነኛውንም መሥዋዕት በመክፈል የወያኔን አገዛዝ ከመታገል በቀር ሌላ አማራጭ ባለመኖሩ የኢሕአፓ አባላት ግንባራቸውን ሳያጥፉ ትግሉን እን ደሚቀጥሉ ጉባዔው ለኢትዮጵያ ሕዝብ አረጋግጧል።

ኢትዮጵያ ሀገራችን በነፃነቷ ለዘለዓለም ትኖራለች!

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢ. ሕ . አ. ፓ)

ጥቅምት 19/2000 ዓ.ም.

---

EPRP
P.O.Box 73337
Washington D.C. 20056
USA
Tel: (202)-291-4217
Fax: (202)-291-7645
E-mail: ESPIC@aol.com

EPRP
BP 22
Bois Colombes 92270
FRANCE

EPRP
Postbus 1253
1000 BG Amsterdam
HOLLAND

Website: http://www.EPRP.com